# የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)

**Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)**

www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com


## የህዝብ እልቂት መሰረታዊ ምክንያት የማግስት ግፍና ግደየሌሽነት ነው

መጋቢት 4፣ 2009 (ሜርች 13፣ 2017)

በትላንትናው እለት በሀገራችን ኢትዮጵያ ዋና ከተማ በአዲስ አባባ እጅግ ዘግናኝ እልቂት ተፈጽሟል።

የሚለስ የሚቀመጥ የሌላቸው ፣ በከፍተኛ ስቃይ ወስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያወያን ይኖሩበት የነበረው የቆሻሻ ክምር ተደርምሶ ከስልሳ በላይ ወገኖቻችን በህይወት ተቀብረዋል። የስርአቱ ባለስልጣኖች ያሙት 60 ግለሰቦች እንደሞቱ ይሆን እንጂ እወነተኛው ቁጥር ግን ከተባለው በላይ እጅግ ብዙ እንደሚሆን ይጠበቃል።

የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ በትላንትናው እለት ህይወታቸው በጠፋው ወገኖቻችን መክንያት የተሰማውን ሀዘን እየገለጸ ለሟቾች ወዳጅና ዘመዶችም ጽናቱን ይመኛል።

ከአንድ ማግሰት መሰረታዊ ተግባሮች ወስጥ የመጀመሪያው የሚሆነው የሚያሰተዳድረወን ህዝብ በህይወት ለመኖር አሰፈላጊና መሰረታዊ የሆኑትን ማለትም ምግብ መጠለያ የመሳሰሉትን እንደሟሉ ሚድረግ ነው። ይህ ደግሞ ችሮታና የበጎ አድራጎት ስራ ሳይሆን የማግስት ግዴታ ነው። የሰው ልጆችም፣ ሰው በመሆናቸው ብቻ ሊከበሩላቸው የሚገባው መሰረታዊ ሰብአዊ መብት ነው።

አንድ ማግሰተ ለህዝቡ እነዚህን መሰረታዊ ጉዳዮች ሳያሟላ ማግስታዊ ሀላፊነቴን ተወጥቻለሁ ማለቱ አሳፋሪና ባዶ ጩኸት ነው።

ህወሀት/ ኢህአዴግ የሀገሪቱን ማግስታዊ ስልጣን ከተቆጣጠረ እነሆ 26 አመት ሆኖታል። ታዲያ በዚህ ጊዜ ሁሉ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በ10 እና በ12 ፐርሰንት አሳደገኩ ይበል እንጂ የሀገራችን ህዝብ ደህው ይበልጥ ደሀ እየሆነ ነው የመጣው። በትላንትናው እለት በቆሻሳሻ ታፍነውና በእሳት ተቃጥለው ለሞቱት ወገኖቻችን ግን ያተረፈው አንዳችም ጥቅም የለም። ይህ የሚያሳየው ኢኮኖሚው አደገል ቢባል እንኳ፣ ተጠቃሚ የሆኑት የህወሀት/ ኢአአዴግ ባለስልጣኖችና ሸሪኮቻቸው እንጂ ብዙሀኑ የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይም ደህው እንዳልሆነ ነው። ማንም የሚዩክደው ሀቅ ዛሬ የህወሀት/ ኢህአዴግ ባለስልጣኖች ደንገት ባለ ሚሊዮን ዶላር ባለሀብት የብዙ ህንጻና ፋብሪካወች ባለንብረት ሆነዋል። ይህ ሁሉ የሚሆነው ከሌላው ኢትዮጵያዊ በሚዘረፍ ሀብትና ንብረት ከደህው ህዝብ አፍ በሚነጠቅ ንብረት ነው። ብዙዎቹም ለዚህ ዓይነት ኑሮ የዳረጋቸው ማግስት ራሱ ሜሬታቸውን ነጥቆ ያለ ተገቢ ካሳ ስላባረራቸው ነው።

በትላንትናው እለት ህይወታቸው የጠፋው ወገኖቻችን እጅግ አደገናኛና ጤነማ ባልሆነ ሁኔታ ወስጥ እንደሚኖሩ ወይም በዚህ ቦታ ምግብና መጠለያ ይፈልጉ እንደነበር ይህ ማግስት ለ26 አመታት ያወቃል። በዚህ ጊዜ ሁሉ የነዚህን ወገኖቻንንን ኑሮ ለማሻሻል፤ በዚህ አደገኛ ቦታም ሊደርስባቸው የሚችለወን አደጋ ገምቶ ካደጋ ለመከላከል ማግስት የወሰደው አንዳችም እርምጃ አልነበረም። ይህ ደግሞ የህወሓት/ኢህአዴግ ማግሰት ለህዝበ ስቃይ፣ ለህዝብ ደህንነት ግድ የሌሽነቱን ቁልጭ አድርጎ ያመለካታል።

በዚህ የማግሰት ግደየለሽነት ለደረሰው ጥፋት በሀላፊነት ተጠያቂ አድርገን የምንይዘው በስልጣኑ ላይ ያለወን ማግስት እንደሆነ ማከወቅ እንወዳለን። ለእኛ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ህይወት እኩል ዋጋ አለው። የሁሉንም ህይወትና ደህንነት ማጠበቅ ከሁሉም በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው።

ይህ ስርአት ከ26 አመት ማግስታዊ ስልጣን በኋላ ዛሬም ለህይወት መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ለህዝብ ማቅረብ አልቻለም። ባላፈው አመት 10 ሚሊዮን ኢትዮጵያዊያን በርሀብ ሲገረፉ ነበር ። አሁን ደግሞ ስደስት ሚሊዮን ኢትዮጵያወያን በተመሳሳይ ረሀብ እየተሰቃዩ ይገኛሉ። ኢትዮጵያወያን ከምን ግዜወም በላይ በተደጋጋሚ በረሀብ የተሰቃዩት በዚህ ስርአት ወስጥ ነው። ባጠቃላይ ስርአቱ መሰረታዊ ሀላፊነቱን መወጣት አቅቶታል።

የዜጎቹን ህይወት ማታደግ የማይችል ማግስት በስልጣኑ ለመቆየትም የሞራል ብቃት የለወም።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)


Tel: 44 7937600756 , +1 9168486790 E-mail : shengo.derbiaber@gmail.com